የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
MINISTRY OF CIVIL SERVICE

ቁጥር ሬ-ቡ-ሀ/98/መ10/9/25
Ref.No.
ቀን 08/09/2005
Date

ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

የትምህርት ሚኒስቴር መጋቢት 20 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር 7/ጠ-259/2612/05 በተጻፈ ደብዳቤ ከሶስት እስከ አምስት ዓመት የትምህርት ቆይታ ጊዜ በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቀው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመምህርነት የሚቀጠሩ ሙያተኞች መነሻ ደመወዝ እንዲሻሻል ባቀረበው ጥያቄ ላይ አስተያየት እንዲቀርብ መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር መ/90-1034/3 በተጻፈ ደብዳቤ መታዘዙ ይታወሳል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት የአካዳሚክ ሙያዎች ሰባት የዕድገት መሰላሎች አሉት፡፡ ከእነዚህ መካከል እስካሁን ባለው አሠራር ረዳት ምሩቅ I እና ረዳት ምሩቅ II የዕድገት መሰላሎች እንደአጻጻፋቸው ቅደም ተከተል ትምህርታቸውን በ4 እና በ5 ዓመት የዩኒቨርስቲ ቆይታ የሚያጠናቅቁ ሙያተኞች መቀጠሪያ ናቸው፡፡ ረዳት ምሩቃኑ በእነዚህ ደረጃዎች ላይ ለአንድ የትምህርት ዓመት ብቻ እንዲቆዩባቸው የሚደረግ በመሆኑ ከመነሻ ደመወዝ በስተቀር የዕርከን ደመወዞች እንዲኖራቸው አልተደረገም፡፡ (የአካዳሚክ ሙያተኞች የደመወዝ ስኬል አባሪ -1 ሆኖ ተያይዟል፡፡)

ሶስተኛው የአካዳሚክ ሙያተኞች የዕድገት መሰላል ረዳት ሌክቸረር የሚል ሲሆን፣ ይህ የአካዳሚክ ማዕረግ ሙያተኞቹ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት አጠናቀው ሌክቸረር እስኪሆኑ ድረስ የሚቆዩበት ነው፡፡

በቅርብ ጊዜ ወዲህ በትምህርት ፕሮግራሞች የመቆያ ጊዜ ላይ በተደረገ የቆይታ ጊዜ ማስተካከያ የአንዳንድ የትምህርት ዓይነቶች የትምህርት ላይ ቆይታ ጊዜ ከ4 ዓመት ወደ ሶስት ዓመት እንዲያጥር ተደርጓል፡፡ ይህንኑ ተከትሎ ምሩቃኑ የትምህርት ላይ ቆይታ ጊዜያቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባ የመነሻ ደመወዝ ማስተካከያ እንዲደረግላቸው ጥያቄ እያቀረቡ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ትምህርት ሚኒስቴርም ይህንኑ ጥያቄ መነሻ በማድረግ ለምሩቃኑ የመነሻ ደመወዝ ማስተካከያ ጥያቄ ማቅረቡ ታውቋል፡፡

*የቀረበው ጥያቄ በዝርዝር ሲፈተሽ፦*

- በተደረገው የትምህርት ላይ ቆይታ ጊዜ ማሻሻያ ትምህርታቸውን በሶስት ዓመት በማጠናቀቅ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአካዳሚክ ባለሙያነት የሚቀጠሩ ምሩቃን የአካዳሚክ ማዕረግ ረዳት ምሩቅ I እንዲሆን፣

- በአዲሱ የትምህርት ማሻሻያ ፕሮግራም የአራት ዓመት ትምህርት አጠናቀው በመመረቅ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአካዳሚክ ባለሙያነት የሚቀጠሩ የአካዳሚክ ማዕረጋቸው ረዳት ምሩቅ II እንዲሆን፣

የሚል ነው፡፡

ይህ ጥያቄ ተቀባይነት ቢያገኝ በአዲሱ የትምህርት ፕሮግራም በአራት ዓመት ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁ ምሩቃንና ከቀድሞ ጀምሮ በአምስት ዓመት የትምህርት ላይ ቆይታ ጊዜ ተመርቀው በረዳት ምሩቅ II ደረጃ ሥራ ይጀምሩ ከነበሩ የህግ እና የምህድስና ሙያተኞች ደረጃ ጋር ስለሚደረብ ወደ ረዳት ሌክቸረርነት ከፍ ማድረግን ይጠይቃል፡፡

ይህም በተራው በስድስት ዓመት የትምህርት ላይ ቆይታ በረዳት ሌክቸረር ደረጃ ሥራ ይጀምሩ የነበሩ የዲቪ.ኤም ምሩቃን ደረጃና የአምስት ዓመት የትምህርት ቆይታ ያላቸውን የምህንድስና ምሩቃን ደረጃ እኩል እንዲሆን ስለሚያደርግ ሌላ የማሻሻያ ጥያቄ ከሙያተኞቹ ሊቀሰቅስ እንደሚችል እንገምታለን፡፡ የደመወዝ ስኬሉ 4ኛ የዕድገት መሰላል የሆነው ሌክቸረር የአካዳሚክ ማዕረግ ግን የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃንን የማያስተናግድ እና ቢያንስ በአንድ የትምህርት መስመር የሁለተኛ ዲግሪ መያዝን ስለሚጠይቅ ተጨማሪ ሽግሽግ ማድረግ አያስችልም፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የደመወዝ ስኬል ደረጃዎች ብዛት አጭር በመሆኑ ይህን ዓይነት የተጠጋጋ ልዩነት ለማስተናገድ አመች አይደለም፡፡ በእንዲህ ዓይነት የደመወዝ ስኬል ደረጃን በሚመለከት የሚፈጠርን አንድ ችግር ለመፍታት የሚወሰድ እርምጃ ሌላ ችግር ሊያስከትል ይችላል፡፡ ስለዚህ የትምህርት ጊዜ ቆይታን አስመልክቶ ስለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን የአካዳሚክ ስያሜ አሰጣጥ ለቀረበው ጥያቄ ከዚህ ቀጥሎ ያለው አስተያየት ቀርቧል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት Office of the Prime Minister

በአሁኑ ጊዜ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መስፋፋት ምክንያት የአካዳሚክ ሙያተኞች እጥረት መከሰቱ እንዲሁም በአገሪቱ በመካሄድ ላይ ባለው መጠነ ሰፊ የኮንስትራክሽን ግንባታ ሥራ ምክንያትም በተለይ በምህንድስና ሙያ መስክ ከፍተኛ የሙያተኛ እጥረት መኖሩን በማገናዘብ የመምህራን አለመሟላት የመማር ማስተማሩን ሂደት ስለሚያስናክል ወቅታዊ መፍትሄ ሊሰጠው የሚገባ ችግር እንደሆነ ታምኖበታል።

በመሆኑም በሚደረገው የደረጃ ሽግሽግ የአምስት ዓመት የትምህርት ቆይታ ጊዜ ያላቸው ምህንድስና/ህግ ምሩቃን እና የስድስት ዓመት የትምህርት ላይ ቆይታ ጊዜ ካላቸው የዲቪ.ኤም ሙያተኞች ጋር መደራረብ ሌላ ችግር የሚቀሰቅስ መሆኑ ከወዲሁ ቢታወቅም አጠቃላይ የደመወዝ ስኬል ስርዓቱ ሲለወጥ ችግሩ እንደሚቃለል በማመን ለጊዜው ችግሩ በዘላቂነት እስኪፈታ፡-

- የሶስት ዓመት የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን ረዳት ምሩቅ I ፣
- የአራት ዓመት የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን ረዳት ምሩቅ II፣
- የአምስት ዓመትና በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን ደረጃ ረዳት ሌክቸረር፣

እንዲሆን ይህንን አስተያየት ለውሳኔ ማቅረባችንን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

ምስራቅ መኮንን (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ

ለክቡር በምክትል ጠቅላይ ሚ/ር ማዕረግ
የመልካም አስተዳደር ሪፎርም ክላስተር
አስተባባሪና የሲ.ሰ.ሚ/ር ሚኒስትር
ለክብርት ሚ/ር ዴኤታ ጽ/ቤት
ለሰው ሀብት ሥራ አመራር ጥናት ዳይሬክቶሬት
ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

☎251-11-553133
Fax 251-11-1550877
✉1367

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
**የትምህርት ሚኒስቴር**

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Education

ቀን
Date 21-9-05

ቁጥር
Ref 23/መ.259/3480/05

አዲስ አበባ
ADDIS ABABA

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
<u>አዲስ አበባ</u>
ለሐረማያ ዩኒቨርሲቲ
<u>ሐረማያ</u>
ለሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ
<u>ሀዋሳ</u>
ለመቀሌ ዩኒቨርሲቲ
<u>መቀሌ</u>
ለመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ
<u>ባሌ ሮቤ</u>
ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ
<u>ሚዛን</u>
ለአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ
<u>አርባ ምንጭ</u>
ለሠመራ ዩኒቨርሲቲ
<u>ሠመራ</u>
ለአክሱም ዩኒቨርሲቲ
<u>አክሱም</u>
ለአዳማ ዩኒቨርሲቲ
<u>አዳማ</u>
ለወላይታ ዩኒቨርሲቲ
<u>ወላይታ ሶዶ</u>

ለወለጋ ዩኒቨርሲቲ
<u>ነቀምት</u>
ለወሎ ዩኒቨርሲቲ
<u>ደሴ</u>
ለደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ
<u>ደብረ ብርሃን</u>
ለደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
<u>ደብረ ማርቆስ</u>
ለድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ
<u>ድሬዳዋ</u>
ለዲላ ዩኒቨርሲቲ
<u>ዲላ</u>
ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ
<u>ባህር ዳር</u>
ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ
<u>ጎንደር</u>
ለጅማ ዩኒቨርሲቲ
<u>ጅማ</u>
ለጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ
<u>ጅግጅጋ</u>
ለአምቦ ዩኒቨርሲቲ
<u>አምቦ</u>

ለአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ
<u>አዲስ አበባ</u>
ለአዲግራት ዩኒቨርሲቲ
<u>አዲግራት</u>
ለደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ
<u>ደብረ ታቦር</u>
ለወልድያ ዩኒቨርሲቲ
<u>ወልድያ</u>
ለወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ
<u>ወልቂጤ</u>
ለዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ
<u>ሆሳዕና</u>
ለመቱ ዩኒቨርሲቲ
<u>መቱ</u>
ለቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ
<u>ቡሌ ሆራ</u>
ለአሶሳ ዩኒቨርሲቲ
<u>አሶሳ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የምሩቃንን ደመወዝ አከፋፈል ስለመግለጽ፡፡</u>

ከላይ በርዕሱ ስለተጠቀሰው ጉዳይ የአዲስ ምሩቃን ደመወዝ እንዲሻሻል በተጠየቀው መሠረት

- የሶስት ዓመት የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን ረዳት ምሩቅ I
- የአራት ዓመት የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን ረዳት ምሩቅ II
- የአምስት ዓመትና በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን ደረጃ ረዳት ሌክቸረር

እንዲሆን የተወሰነ መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በ09/09/2005 በቁጥር መ/90-1034/4 የተፃፈ ደብዳቤ ገልጾልናል፡፡

ስለሆነም ለአፈፃፀም ያመች ዘንድ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አጥንቶ የሰጠውን አስተያየት ጭምር በጠቅላላው 6 ገጽ ማብራሪያና የደመወዝ ስኬል ፎቶ ኮፒ አያይዘን የላክን ስለሆነ አዲስ ተሻሽሎ የተፈቀደው የአካዳሚክ ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል ከግንቦት 1 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

[signature]

ከበ ኦርጌሳ ዲንሳ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለክቡር ም/ጠ/ሚኒስትርና የትምህርት ሚኒስትር /ከ6 ገጽ አባሪ ጋር/
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ /ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ/ከ6 ገጽ አባሪ ጋር/
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ /አጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ/ከ6 ገጽ አባሪ ጋር/
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ /ቴ/ሙ/ት/ስ/ዘርፍ/ከ6 ገጽ አባሪ ጋር/
- ለሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ /ከ6 ገጽ አባሪ ጋር/
- ለሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከ6 ገጽ አባሪ ጋር/
- ለፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት /ከ6 ገጽ አባሪ ጋር/

<u>ትምህርት ሚኒስቴር</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Education

☎ 011 1 55 31 33,
✉ 1367
ፋክስ (Fax) 011 1 57 06 86, 55 08 77

ቁጥር 7/ጠ259/8ር59/01
Ref. No
ቀን 5/13/01
Date

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
ADDIS ABABA - Ethiopia

ዝርዝራቸው ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ለተደረገ ዩኒቨርስቲዎች
በያሉበት

ጉዳዩ፡ አንደኛ ዲግሪ ይዘው ከስራው ዓለም በረዳት ምሩቅነት ስለሚቀጠሩ ደረጃ አሰጣጥ እና ከረዳት ምሩቅ I ወደ ረዳት ምሩቅ II ለሚደረግ ዕድገት የአገልግሎት ዘመንን መተርጎም ላይ የተሻሻለ መመሪያ

ከስራው ዓለም በረዳት ምሩቅነት ስለሚቀጠሩ ደረጃ አሰጣጥን በሚመለከት በተላለፉት ሁለት መመሪያዎች መካከል መታረም ያለበት ክፍተት አለ፡፡ በአገልግሎት ዘመን ትርጉም አሰጣጥ ላይ ያልጠሩ ብዥታዎችና አዳዲስ ጥያቄዎችም ይታያሉ፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩ በመንግስት ባጀትም መወሰን ስለሆነ በተቋማት መካከል ተመሳሳይ አፈጻጸምን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ስለሆነም በርእሰ ጉዳዩ ላይ የተብራራ አንድ ወጥ መመሪያ ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆንዋል፡፡ በዚህ መስረትም የሚከተለው ማሻሻያ ተፈጻሚ እንዲሆን ተወስንዋል፡፡

(1) ከስራው ዓለም በረዳት ምሩቅነት በትምህርት ሚኒስቴር ወይም በትምህርት ሚኒስቴር እውቅና የሚመደቡት ዜጎች በስራው ዓለም በተመረቁበት ሙያ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ ያገለገሉ ከሆነ የረዳት ምሩቅ II ደረጃና ደሞዝ ያገኛሉ፤ ካልሆነ ግን በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር (5) እና (6) በተቀመጡት የተለዩ አገባቦች የማይሸፈኑት ሁሉ የረዳት ምሩቅ I ደረጃና ደሞዝ ያገኛሉ፡፡ ሁለት ዓመት ማለት ደግሞ ሁለት ሙሉ የካላንደር ዓመታት ማለት ነው፡፡

(2) ከስራው ዓለም በረዳት ምሩቅነት የሚመደቡት ዜጎች የአገልግሎት ዘመናቸው ሲሰላ የመጀመሪያው ዲግሪ ካገኙ በኃላ የሰጡትን አገልግሎት እንጂ ከዚያ በፊት የሰጡትን አገልግሎት ታሳቢ አይሆንም፡፡

(3) ከአገልግሎት ዘመን አንጻር ሲታይ በረዳት ምሩቅ I የተመደቡ ዜጎች ወደ ረዳት ምሩቅ II ሊያድጉ የሚችሉት ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ለዩኒቨርስቲው አንድ ሙሉ የካላንደር ዓመት አገልግሎት የሰጡ ከሆነ ነው፡፡

(4) የረዳት ምሩቅ I ደረጃ ያላቸው አገልግሎት ዘመናቸውን ሳያምዋሉ የድህረ ምረቃ ትምህርት ዕድል ያገኙ ረዳት ምሩቃን ትምህርታቸውን አጠናቀው የሌክቸረር ማዕረግ እስኪያገኙ ድረስ በያዙት የረዳት ምሩቅ I ደረጃ ይቀጥላሉ፡፡ ሆኖም የማስትሬት ዲግሪ ኮርስ ጨርሰው thesis መጻፍ ሳይገደዱ በቀጣሪው ዩኒቨርስቲ ፍቃድና እውቅናም የዶክትሬት ዲግሪ ፕሮግራምን እንዲቀጠሉ ከተደረገ ተገቢውን ውል መፈረም እንዳለባቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሌክቸረር ማዕረግ ሳይሰጣቸው ወደ ዶክትሬት ፕሮግራም ከተዛወሩበት ጊዜ ጀምሮ የሌክቸረር ደሞዝና ተዛማጅ ጥቅሞች ሊከፈላቸው ይችላል፡፡

(5) የረዳት ሌክቸረር ማዕረግና ደሞዝ ለዩኒቨርስቲው በተሰጠ አገልግሎትና የስራ ውጤታማነት መሠረት በዩኒቨርስቲው ስርዓትና አሰራር ከሚሰጥ በስተቀር በሌላ መስሪያ ቤት በተሰጠ አገልግሎት ምክንያት ይገባኛል የሚባልበት አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል ዩኒቨርስቲዎች አንደኛ ዲግሪ ላላቸው አዲስ ተቀጣሪዎች የሚሰጡት የረዳት ሌክቸረር ደረጃ አሰጣጥ ነባር ስርዓት (ለምሳሌ ለሃኪሞች) ቢኖር የሚቀጥል ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ሙያዎችና የትምህርት ደረጃ ከስራው ዓለም የሚመደቡትም የአገልግሎት ዘመናቸው ግምት ውስጥ ሳይገባ የረዳት ሌክቸረር ማዕረግና ደሞዝ ያገኛሉ፡፡

(6) ከዚህ በፊት ስለጉዳዩ የተላለፉ መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

(7) ይህ የተሻሻለ መመሪያ ከመስከረም 1 ቀን 2002 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

ከሠላምታ ጋር

አድሃና ሃይለ አድሃና (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ቅጂ/ ለክቡር የትምህርት ሚኒስትር
ለትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
ለመምህራን ልማት የስራ ሂደት
ለረዳት አማካሪዎች ቡድን
ለፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደር የስራ ሂደት
ትምህርት ሚኒስቴር

ለሀረሚያ ዩኒቨርስቲ

ለሃዋሳ ዩኒቨርስቲ

ለመቀሌ ዩኒቨርስቲ

ለመደወላቡ ዩኒቨርስቲ

ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ

ለሰመራ ዩኒቨርስቲ

ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ

ለአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ለአክሱም ዩኒቨርስቲ

ለአዳማ ዩኒቨርስቲ

ለወለጋ ዩኒቨርስቲ

ለወሎ ዩኒቨርስቲ

ለደብረ ብርሃን ዩኒቨርስቲ

ለድሬድዋ ዩኒቨርስቲ

ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ

ለዲላ ዩኒቨርስቲ

ለባህር ዳር ዩኒቨርስቲ

ለጐንደር ዩኒቨርስቲ

ለጅማ ዩኒቨርስቲ

ለጅጅጋ ዩኒቨርስቲ

ለአምቦ ዩኒቨርስቲ

<u>በያሉበት</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ
የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

Federal Democratic Republic of
Ethiopia
Ministry of Health

ቀን 14/10/2010
Date
ቁጥር ... /15/39/322
Ref. No.

**ለደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ**

**<u>ደብረማርቆስ፣</u>**

**ጉዳዩ:- <u>የጤና ባለሙያዎች የወጪ መጋራት ሥራ ሙሉ በሙሉ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንዲሰራ ስለማሳወቅ፣</u>**

በተሻሻለው የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት መመሪያ መሠረት ተራ ቁጥር 8 በፊደል ተራ "በ" በአገልግሎት ግዴታቸውን የተወጡ ባለሙያዎች አገልግሎት ከሰጡበት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሚያቀርቡት የአገልግሎት ማረጋገጫ መሠረት በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከዕዳ ነጻ ስለመሆናቸው ከባለሥልጣኑ ማስረጃ በማቅረብ ከሰለጠኑበት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የትምህርት ማስረጃቸውን ማግኘት እንደሚችሉ የትምህርት ሚኒስቴር በ29/12/2009 ዓ.ም በቁጥር7/ጠ259/11179/35 በአድራሻ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲጽፍ ለዩኒቨርስቲአችሁ መመሪያውን ማስተላለፉ ታውቋል፡፡

ሆኖም የሚፈለግባቸውን የወጪ መጋራት በአገልግሎት ግዴታቸውን የተወጡ እና በክፍያ ግዴታቸውን ለመወጣት ጥያቄ ለሚያቀርቡ ሐኪሞች ሆነ ሌሎች የጤና ባለሙያዎች መመሪያው ከተላለፈ በኋላ አንዳንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እዚያው መፈጸም ሲገባቸው እስካሁን ባለሙያዎችን ወደ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እየላኩ በመሆኑ በዚያው እንዲሰራ ማሳሰብ አስፈልጓል፡፡

እንደሚታወቀው በደንብ ቁጥር 154/2000 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት መመሪያ ላይ አንቀጽ 11 ተራ ቁጥር 2 የወጪ መጋራትን በገንዘብ ግዴታን ለመወጣት አጠቃላይ ክፍያውን የመሰብሰብ ፣የመከታተልና የመቆጣጠር ሃላፊነት ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተሰጠ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ስለሆነም የወጪ መጋራትን በክፍያ ለመወጣት ሐኪሞች ጥያቄ ሲያቀርቡ ከላይ በደንቡ ከተገለጸው ውጭ ሊከፍሉ የሚገባውን ወጪ በመሥሪያ ቤታችን አስልቶ ለክፍያ ለገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ሲላክ የቆየው አሰራር መቆም እንዳለበት ታምኗል፡፡ በመሆኑም የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከሰኔ 18 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ በአባሪው ላይ በተገለጸው መሠረት በዩኒቨርስቲው/በኮሌጁ በኩል አስፈላጊው እንዲፈጸም እየገለጽን፣ ግዴታቸውን በአገልግሎት የተወጡትን ሆነ በክፍያ ለመወጣት የሚፈልጉትን ሐኪሞች ሆኑ ሌሎች የጤና ባለሙያዎች ወደ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እንዳይላኩ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ህብታሙ ደምሴ ደበላ
የሰው ሀብት አስተዳደር
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ
ደብዳቤው የተጻፈበት ቀን 14/10/10
ደብዳቤው የደረሰበት ቀን 22/10/10

ግልባጭ

- ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
- ለኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስ/ቁ/ባለሥልጣን
  <u>አዲስ አበባ፣</u>
- ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለክብርት ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት/ሪፎርምና አስተዳደር ዘርፍ
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት/ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት/ፕሮግራም ዘርፍ
- ለሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
  <u>ጤና ጥበቃ፣</u>

251-(0)11-5517011 251-(0)11-5515425 251-(0)11-5159869 251-(0)11-5518031
Fax 251-(0)11-5519366 251-(0)11-5159657 251-(0)11-5524549
E-mail:moh@ethionet.et
Web site: www.moh.gov.et
1234 Addis Ababa, Ethiopia

## ሐኪሞች ሆኑ ሌሎች የጤና ባለሙያዎች የትምህርት ማስረጃ እና የሙያ ፈቃድ ለመውሰድ ጥያቄ ሲያቀርቡ ያለው አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል፣

በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በተላለፈው የሐኪሞች ኮስት ሞዴል መመሪያ እያንዳንዱ ዩኒቨርስቲ በመማር ላይ ያሉ ፣ያቋረጡ ወይም የተመረቁ ተማሪዎችን ወጪን እያሰሉ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እንዲያስተላልፉ ፣የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በተለይ በገቡት ውለታ መሠረት ግዴታቸውን የማይፈጽሙ ተጠቃሚዎች ሲከፍሉ በሞዴሉ መሠረት የተሰላውን ጠቅላላ ወጪና ቅጣት እንዲከፍሉ እንዲያደርግ በ30/10/2001 ዓ.ም በቁጥር7/ጠ-259/1797 በተጻፈ ደብዳቤ በጥብቅ ማሳሰቡ ተገልጿል፡፡

በመሆኑም፡-

1. በመሥሪያ ቤታችንም ሆነ በክልል ጤና ቢሮዎች/በፌዴራል ሆስፒታሎች እና በሌሎች የመንግሥት ሆስፒታሎች የሀኪሞችን ወጪ አስልቶ ክፍያ እንዲፈጸም ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጥያቄ የማቅረቡ አሰራር እንዲቆም፣ የክፍያው ስሌት በዩኒቨርስቲዎችና በገቢዎች ባለስልጣን የሚፈጸም መሆኑ እንዲታወቅ፣

2. የከፍተኛ ትመህርት ተቋማት ከወጪ መጋራት ጋር በተያያዘ ግዴታቸውን በአገልግሎት የተወጡትን ሐኪሞች ሆኑ ሌሎች የጤና ባለሙያዎች ያገለገሉበትን ጊዜ (ከ-እስከ-) ቀን ወርና ዓ.ም በመጥቀስ የትምህርት ማስረጃቸውን ከተማሩበት ዩኒቨርስቲ ማግኘት እንዲችሉ ለኢትዮጵያ/ለቅርንጫፍ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በደብዳቤ ሲገለጽ፣ በኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስ/ቁ/ባለሥልጣን የሙያ ፈቃድ በሚሰጥባቸው ሙያ ለተመረቁት ብቻ ሙያ ፈቃዳቸው እንዲሰጣቸው ለባለሥልጣኑ በቅጂ ማሳሰብ፣

3. ለተወሰነ ጊዜ አገልግለው ቀሪውን የአገልግሎት ጊዜ በገንዘብ ለመክፈል ለሚፈልጉት ሐኪሞች ሆኑ ሌሎች የጤና ባለሙያዎች ያገለገሉበትን ጊዜ (ከ-እስከ-) ቀን ወርና ዓ.ም እና የሚቀራቸውን የአገልግሎት ጊዜ በመጥቀስ የወጪ መጋራትን ከነመቀጫው ለኢትዮጵ/ በቅርንጫፍ ለሚገኙ/ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን እንዲከፍሉ ደብዳቤ ሲጻፍ የሚፈለግባቸውን ገንዘብ ለመክፈላቸው የሚያረጋግጥ ደረሰኝና ደብዳቤ ሲሰጣቸው በኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስ/ቁ/ባለሥልጣን የሙያ ፈቃድ በሚሰጥባቸው ሙያ ለተመረቁት ብቻ ማስረጃውን ማቅረባቸውን እያረጋገጠ ሙያ ፈቃዳቸው ሊሰጣቸው እንደሚችል ለባለሥልጣኑ በቅጂ ማሳሰብ፣

4. ባጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የወጪ መጋራትን በተመለከተ በመንግሥት ወጪ ተምረው በሚኒስትሩ መሥሪያ ቤት የተቀጠሩትን የጤና ባለሙያዎች ሆኑ የድጋፍ ሰጪ የሆኑ ሠራተኞች እና አዲስ ተመርቀው ለመመደብ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው በክፍያ ግዴታቸውን ለመወጣት ጥያቄ የሚያቀርቡትን አለመመደባቸውን በመጥቀስ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚፈለግባቸውን ገንዘብ ከነመቀጫው እንዲከፍሉ የማድረግ፣

5. **የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አሟልተው የሚልኩአቸው ማስረጃዎችን በተመለከተ፣**

5.1 ግዴታቸውን በአገልግሎት የተወጡ ሆኑ ለተወሰነ ጊዜ አገልግለው ቀሪ የሚፈለግባቸውን የአገልግሎት ግዴታ በክፍያ ለመወጣት የሚፈልጉ የጤና ባለሙያዎች ከመቼ እስከ መቼ በሙያቸው እንደሰሩ ተገልጾ፣ በተጨማሪ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኩል የተመደቡበት ደብዳቤ፣ በሚሰሩበት ቦታ የተቀጠሩበት ደብዳቤ፣ ከሌላ ቦታ ተዛውረው ከሆነ የዝውውር ደብዳቤ አባሪ ተደርገው በሽኚ ደብዳቤ እንዲላክ፣

6. በአገልግሎት የማይያዝ ማስረጃን በተመለከተ፡-

5.1 በተሻሻለው የከፍተኛ የወጪ መጋራት መመሪያ መሠረት ጤና ጥበቃ ሚ/ር ሳይመድበው በገዛ ፈቃዱ በመንግሥት የጤና ተቋም የተፈጸመ የጤና ባለሙያ አገልግሎት በሥራ ልምድነት ለወጪ መጋራት የማይያዝ ስለሆነ እንዲህ ዓይነት አገልግሎት ስሌት ውስጥ እንዳይካተት እንዲደረግ፣

5.2 የተወሰነ ጊዜ አገልግሎ ለድህረ ምረቃ ትምህርቱን የሚከታተል የጤና ባለሙያ በትምህርት ላይ የቆየበት ጊዜ በሥራ ልምድነት ለወጪ መጋራት የማይያዝ ስለሆነ ግዴታን በመፈጸም ስሌት ውስጥ እንዳይካተት፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5.2 ድረስ በዝርዝር የተጠቀሱት ተግባራት በአግባቡ ተፈጻሚ እንዲደረጉ እናሳስባለን፡፡